11ኛ ዓመት ቁጥር 25
11th Year Nº

ባህር ዳር ሐምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar 21st July, 2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ-ሕግ

ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር Price	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር 40/1998 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	Regulation No. 40/2006 The Amhara National Regional State Dessie Business and Management College Establishment, Council of Regional Government Amendment Regulation.

ደንብ ቁጥር 40/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

REGULATION NO.40/2006

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE DESSIE BUSINESS AND MANAGEMENT COLLEGE ESTABLISHMENT REGULATION OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

ከታሪክ በመነጨ ምክንያትና የአካባቢውን ሕብረተሰብ ፍላጐት መሠረት በማድረግ የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅን ስያሜ መለወጥና በአዲስ መተካት በማስፈለጉ፤

ይህንኑ መፈፀም የሚቻለው ደግሞ ኮሌጁ የተቋቋመበትን ደንብ በማሻሻል ብቻ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና የክልሉን ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማስፋፊያ ኤጀንሲ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 87/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 15 ድንጋጌዎች በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

WHEREAS, it has been found appropriate to alter or substitute the designation of Dessie Business and Management College due to historical grounds as well as on the basis of the interest of the surrounding community thereof;

WHEREAS, such is in fact accomplished by solely amending the regulation which has established the college;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58 Sub. Art. 7 of the revised Regional Constitution and Art.15 of the Regional Technical and Vocational Education and Training Agency Establishment Proclamation No. 87/2003, (as amended), hereby issues this regulation as follows.

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 40/1998 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short Title

This regulation may be cited as the "The Dessie Business and Management College Establishment, Council of the Regional Government Amendment Regulation No. 40/2006."

2. ማሻሻያ

የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ የተቋቋመበት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 12/1995 ዓ.ም በዚህ ደንብ ተሻሽሏል፡-

ሀ. የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ ይህ ደንብ ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ የወ/ሮ ስህን ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ በመባል የሚጠራ ይሆናል።

2. Amendment

The Dessie Business and Management College Establishment Council of the Regional Government Regulation No. 12/2003 is hereby amended as follows:

a. The Dessie Business and Management College shall be renamed as Wizero Sihin Business and Management College as of the day, on which this regulation comes into force.

ለ. በቀዳሚው ደንብ ውስጥ ነባሩን ስያሜ የሚጠቅሱ ድንጋጌዎች ሁሉ በዚህ ደንብ መሠረት አዲሱን የኮሌጁን ስያሜ እንደጠቀሱ ሆነው ይቆጠራሉ።

3. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ሐምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም
አያሌው ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ርዕሰ መስተዳድር

b. All provisions in the former regulation citing the previous designation of the college shall be presumed to have been mentioning the new name of the college pursuant to this regulation.

3. Effective Date

This regulation shall came into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 21st day of July, 2006
Ayalew Gobezie
Head of Government of the
Amhara National Regional State